# በአማራ ክልል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ/መከ/መቆ/

# ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

# በወጣቶችና ስነ-ተዋልዶ ላይ የተዘጋጀ ሲምፖዚየም

## ምጥን ቃለ-ጉባዔ

ነሐሴ/2002 ዓ.ም

<u>ባህርዳር፣</u>

## ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 1 | የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት | 2 |
| 2 | የክብር እንግዳው የመክፈቻ ንግግር | 4 |
| 3 | የአጋር አካላት መልዕክት | 6 |
| 4 | የጥምር ኘሮግራሙ አጭር የተግባራት አፈፃፀም ገላፃ | 7 |
| 5 | በቀረቡ የመነሻ ጽሑፎች ላይ የፓናል ውይይት | 14 |
| 6 | የስምፖዚየም ማጠቃለያ ውይይት | 23 |
| 6 | ቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዩች | 27 |
| 7 | የመዝጊያ ንግግር | 30 |

# በአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤት በወጣቶችና ስነ-ተዋልዶ ላይ የተዘጋጀ ሲምፖዚየም

## ምጥን ቃለ-ጉባዔ

- የሲምፖዝየሙ ቀን ከነሐሴ 1-2/2002 ዓ.ም
- የሲምፖዝየሙ ቦታ - ሙሉዓለም ባህል ማዕከል አዳራሽ
- የሲምፖዝየሙ የቆይታ ጊዜ - ሁለት ቀናት

### ተሣታፊዎች

- የክልል ቢሮዎችና የልዩ ልዩ መንግስት መ/ቤት ኃላፊዎች
- የዞንና የወረዳ HAPCO አስተባባሪዎች
- የአጋር አካላት ኃላፊዎች
- የእምነት ተቋማት መሪዎች
- የልዩ ልዩ ማህበራት መሪዎች

### መድረክ መሪዎች

- አቶ ያየህ አዲስ - የክልሉ ወጣቶች ስፖርት ቢሮ ኃላፊ
- አቶ ሙለሰው ልጃለም - የክልሉ ጤና ቢሮ የጤና ማበልፀጊያና በሽታ መከላከል ዋና የሥራ ሂደት

### ጽሑፍ አቅራቢዎች

- ዶ/ር ያለው እንዳወቅ
- ዶ/ር በለጠ ታፈሰ
- አቶ አገኘሁ ገበየሁ
- አቶ ሲሳይ መለሰ

የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤት የህዝብ ግንኙነት ዋና የሥራ ሂደት መሪ የሆኑት አቶ አዳነ በውቀት የኘሮግራም ትውውቅ ካደረጉ በኋላ የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ እሸቴ ግርማን የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት እንዲያስተላልፍ ጋብዘዋል፡፡

## የአቶ እሸቴ ግርማ የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስ/ጽ/ቤት ኃላፊ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት

የተከበሩ አቶ ያየህ አዲስ፡- የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ

- ክቡራን የክልል ቢሮዎችና ልዩ ልዩ መንግስታዊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች፣
- ክቡራን የዞንና የወረዳ አስተዳዳሪዎች
- የተከበራችሁ የልዩ ልዩ አጋር አካላት ኃላፊዎችና ተወካዬች፣
- የተከበራችሁ የልዩ ልዩ እምነት ተቋማት መሪዎች፣
- የተከበራችሁ የልዩ ልዩ ማህበራት መሪዎች፣
- የተከበራችሁ ተጋባዥ እንግዶችና የሲንፖዚየሙ ተሣታፊዎች

ክቡራትና ክቡራን

ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!!

ከሁሉ አስቀድሜ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና በራሴ ስም ወደዚህ ሲንፖዚየም እና ውብ በድንቅ ቅርሳቅርሶች ወደታወቀችው ባህርዳር እንኳን በደህና መጣችሁ እላለሁ፡፡

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና መቆጣጠር ተግባር የበለጠ ተጋላጭና ልዩ ትኩረት ከሚያሻቸው ክፍሎች አንዱ ወጣቶች መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ በወጣቶች ዙሪያ በርካታ ፀረ-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተግባራት በራሳቸው በወጣቶች ሙሉ ተሣትፎና በተለያዩ አጋር አካላት ዘርፈ-ብዙ ምላሽ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

ከነዚህ ኘሮግራሞች መካከል አንዱ በዛሬና በነገው የሲንፖዝየም ውሏችን የምንቃኘው በተባበሩት መንግስታታ የስነ-ሕዝብ ፈንድና በተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መርጃ ድርጅት አጋርነት በክልላችን እየተካሄደ ያለውን የወጣቶች ልማት ጣምራ ኘሮግራም ነው፡፡ ኘሮግራሙ በስድስት ዞኖች በሚገኙ ሰባት ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የተከናወነና የበጀት ምንጩ ከኖርዌይ መንግስት በእርዳታ የተገኘ ሃያ ሚሊዮን ብር ነው፡፡

ኘሮግራሙ ሙሉ በሙሉ በወጣቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ይዟቸው የተነሳው ሰባት ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በወጣቶች ዙሪያ የሚሰሩ ፈፃሚ አካላትን በማስተባበርና የመፈፀም አቅማቸውን በማጎልበት ወጣቶች የሥነ-ተዋልዶ ጤናና የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃና አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡
2. ወላጆችና ህብረተሰቡ ለወጣቶች ፍላጎት ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡና ወጣቶች ራሳቸውን ከፆታዊ ጥቃትና ከሥነ-ተዋልዶ መብት ጥሰት ለመከላከል፣ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ ማከናወን፡፡
3. ወጣቶች የመረጃና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚነት መብት እንዲኖራቸውና እነርሱን አስመልክቶ በሚዘጋጁ የህብረተሰብ አቀፍ የልማት ኘሮግራሞች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡
4. ወጣቶች በተለይም በከፍተኛ ሁኔታ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
5. ወጣት ልጃገረዶች ራሳቸውን ከፆታዊ ጥቃትና ከጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲከላከሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡፡
6. በከፍተኛ ሁኔታ ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች በተለይም ወጣት ልጃገረዶች ላይ ትኩረት በማድረግ በቋሚ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ፡፡
7. አሣታፊ የሆነ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ኘሮግራሙን ከግብ ማድረስና መልካም ተሞክሮዎችንና አበረታች ውጤቶችን ወደ ሌሎች አካባቢዎች በማስፋፋት የልምድ ልውውጥ ማካሄድ፡፡

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ በማድረስ ረገድ የእናንተ ተሣትፎ የጐላ ሰለነበር የተሄደበትን ርቀት በመገምገምና በማስፋት ሂደቱ ላይ በዚህ ሲንፖዚየም የምታደርጉት አስጸዋጽኦ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በመጨረሻም ይህን ሲንፖዚየም እንዲከፍቱልንና የሥራ አቅጣጫ እንዲሰጡልን ክቡር አቶ ያየህ አዲስ የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊና የክልሉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/የሥራ አመራር ቦርድ አባል በአክብሮት እጋብዛለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ!!**

## የአቶ ያየህ አዲስ፡- የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊና የክልሉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ የሥራ አመራር ቦርድ አባል የመክፈቻ ንግግር

- ክቡራን የክልል ቢሮዎችና ልዩ ልዩ መንግስታዊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች፣
- የተከበራችሁ የልዩ ልዩ አጋር አካላት ኃላፊዎችና ተወካዮች፣
- የተከበራችሁ የልዩ ልዩ የእምነት ተቋማት መሪዎች፣
- የተከበራችሁ የልዩ ልዩ ማሕበራት መሪዎች፣
- የተከበራችሁ ተጋባዥ እንግዶችና የሲንፖዚየሙ ተሣታፊዎች

ክቡራትና ክቡራን

የወጣቶችን ሕይወት የተሻለ ለማድረግ በርካታ አበረታች ጅምሮችና ውጤቶች እየታዩ ያሉ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ በአንጻሩ ወጣቶች ዛሬም ያልተቀረፉ በርካታ ችግሮች ያሉባቸው መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው፡፡ ይህን የወጣቶች ችግር ግዝፈትና አሳሳቢነት ከግምት በማስገባት በዚህ ሲንፖዚየም ላይ ውድ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ በመገኘታችሁ በክልላችን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሥራ አመራር ቦርድ ስም ከፍ ያለ ምስጋናየን አቀርባለሁ፡፡

ውድ ተሳታፊዎች

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና በሀገራችን እያደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ ችግር ለመግታት በርካታ ኘሮግራሞች ተቀርፀው ተግባራዊ እየሆኑ ይገኛል፡፡ በተለይም ወጣቶች የችግሩ ዋነኛ ተጠቂ በመሆናቸው መንግስት የወጣቶች ፖሊሲና በርካታ የወጣቶችን ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ያገናዘቡ ስትራቴጅዎችና መርሃ-ግብሮች ቀርጾ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከነዚህ ስትራቴጅዎች መካከል የወጣቶች ሥነ-ተዋልዶ ጤና ስትራቴጅ አንዱ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተጣጣመ በርካታ መርሃ-ግብሮች እየተካሄዱ ሲሆን ከነዚህ ኘሮግራሞች ውስጥ አንዱ በዩኤንኤፍፒኤ እና በየኒሴፍ የጋራ ድጋፍ በክልላችን በሚገኙ 7 ወረዳዎች ውስጥ በወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና እና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል ላይ እየተከናወነ ያለው ጥምር ኘሮግራም ነው፡፡ ኘሮግራሙ በተጀመረባቸው ወረዳዎች ካከናወናቸው ተግባራት ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

1. ወጣቱ የስነ-ተዋልዶ ጤናና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መረጃና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጓል፡፡
2. የወጣቱና የህብረተሰቡን እንዲሁም በወጣቱ ላይ የሚሰሩ ተቋማትን አቅም የመገንባት ሥራ በሰፊው አከናውኗል፡፡
3. ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ የሆኑ ወጣቶች ላይ ተጋላጭነትን የመቀነስና አቅም የማጎልበት ሥራ ሰርቷል፡፡
4. የወጣት ሴቶችን ያለ ዕድሜ ጋብቻ ለመከላከል ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነው የበርካታ ሴቶች ያለ እድሜ ጋብቻ እንዲሰረዝ ማድረግ አስችሏል፡፡
5. ለችግረኛና ወላጆቻቸውን ላጡ ህፃናት በቋሚ የገቢ ማስገኛ ዘዴ ለማሰማራት ያስቻለ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል፡፡ ሌሎችም በርካታ ተግባራት በኘሮግራሙ በመከናወኑ የተሻለ ውጤት የተመዘገበ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ለዚህ ስኬት በየደረጃው የሚገኙ አስፈፃሚዎችና ፈፃሚዎች ሚና የጐላ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ መርሃ ግብር እንዲሳካ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፋችሁትን ሁሉ ለክልላችን ህዝብ ተቆርቋሪነታችሁንና አጋርነታችሁን አረጋግጣችኋልና ከልብ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡ በዚህ ሲንፖዚየም ከእናንተ የሚገኙ ግብዓቶች ለቀጣይ ሥራችን የጎላ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ በመሆኑም የነቃ ተሣትፎ በማድረግ ሲንፖዚየሙን ውጤታማ እንደምታደርጉት እምነቴ የፀና ነው፡፡

በቀጣይም በዚህ ኘሮግራም የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግና መልካም ተሞክሮዎችና ኘሮግራሙ አሁን ካለበት 7 ወረዳ ወደ ሌሎች ለማስፋት እንዲቻል ሁላችንም በየደረጃው የምንገኝ ፈፃሚዎች፣ አስፈፃሚዎችና ለጋሽ ድርጅቶች ያልተቆጠበ ጥረት እንድናደርግ ጥሪዬን በዚህ አጋጣሚ አስተላልፋለሁ፡፡ ይህን ኘሮግራም በተመለከተ የተዘጋጀው ይህ ሲምፖዚየም የተሳካ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ያደረጋችሁትን ሁሉ እያመሰገንኩ ሲንፖዚየሙ በይፋ የተከፈተ መሆኑን አበስራለሁ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡

## አጀንዳ1፡- የአጋር አካላት መልዕክት

የዩኔሰፍ ተወካይ አቶ ፈቃዱ ድርጅታቸው በዚህ ኘሮግራም ላይ ያለውን ተሣትፎና ዓላማዎቹን ዘርዘር አድርገው አቅርበዋል፡፡ በዚህም ፡-

- ድርጅታቸው ከቅርብ ቀን ወዲህ በወጣቱ ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው ለዚህም መነሻ የሆነው በወጣቱ ላይ ድህነት፣ ሥራ አጥነት እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ ችግሮች የተጫጫኑበት በመሆኑና ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭትም መስፋፋት ዓይነተኛ ክፍል በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

- ዩኒሴፍ በወጣቶች ላይ ያለውን ዘርፍ ብዙ ችግር ለመቅረፍ በጥናት በመለየት ኘሮግራም ቀርጾ በመንቀሳቀስ ላይ ነው፡፡ ለዚህም የወጣቶችን ፖኬጅ እንደመሳሪያ በመጠቀም እየሰራ ይገኛል፤ ወደፊትም ይሰራል ካሉ በኂላ ድርጅታቸውም በወጣቱ ላይ የሚያተኩርባቸውን አቅጣጫዎችም ጠቁመዋል፡፡ እነርሱም፡-

    - የህይወት አቅጣጫውን ያወቀ፣ ህይወቱን የሚወድ እንዲሁም ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምንነት ጠንቅቆ የሚያውቅ ትውልድ ማፍራት፣
    - መንግስት የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መደገፍና ማበረታታት፣ ከኖረዌ መንግስት በምናገኘው ድጋፍ የወጣቱን ልማታዊ እንቅስቃሴ መደገፍና ይህንን አጠናክሮ መጠቀል መሆኑን ዘርዘር አድርገው ለተሳታፊው አቅርበዋል፡፡

## የአቶ ይድነቃቸው የዩኤንኤፍፒ (UNFPA) ተወካይ መልዕክት

- ድርጅታችን በክልሉ ውስጥ ድጋፍ ያደርጋል በተለይ የወጣቶች ድምፅ እንዲደመጥ፣ ወደ አመራር እንዲመጡ፣ የውሣኔ ሰጭነት ሚናቸው የጐላ እንዲሆን ይሰራል ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በወጣቶች ላይ የሚከሰተውን ያለዕድሜ ጋብቻ የሚያደርሰውን ችግር በመከላከል ላይም እንደሚሰራ ጠቁመው ከዚህ በተጨማሪ በድህነት ቅነሳው ላይ የወጣቶች ተሣትፎ እንዲኖር፣ ትልልቅ ኮንፈረንሶች በወጣቶች ዙሪያ እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት እንደሚሰራ አውስተው አሁን በሰባት ወረዳ ብቻ ያለውን የወጣቶች ሥነ-ተዋልዶና ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ኘሮግራም ወደ ሁሉም ወረዳዎች የማዳረስ እቅድ እንዳለው ዘርዝረዋል፡፡

## አጀንዳ2፡- የጥምር ኘሮግራሙ አጭር የተግባር አፈፃፀም

በአቶ አዳሙ ዳኜው፡- የጥምር ኘሮግራሙ ኦፊሰር

ይህ ኘሮግራም ከተጀመረ እስከ አሁን ድረስ ምን እንቅስቃሴ ተደረገ የሚለውን አቀርበዋል፡፡ ኘሮግራሙም በሰባት ወዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ማለትም፡- ጎንደር ከተማ፣ ባህርዳር ከተማ፣ በኮምቦልቻ ከተማ፣ በቆቦ ዙሪያ ወረዳ፣ በደራ ወረዳ፣ በባሶሊበንና በእናርጅ እናውጋ ወረዳ ላይ መጀመሩን አውስተዋል፡፡ ለዚህም የተያዘው በጀት ወደ 20 ሚሊዮን ብር እንደሚደርስና ለቀጣይ ዓመታትም ከዚህ ያላነሰ ብር መበጀቱን ለዚህም ፈፃሚ አካላት ኘሮግራሙ የሚዘረጋባቸው ወጣቶችና ስፖርት፣ የሴቶች ጉዳይ፣ የትምህርት እንዲሁም የጤናና የማስታወቂያ ጽ/ቤቶች መሆናቸውንም ገልፀዋል፡፡

ኘሮግራሙ ሰባት ዓላማዎችን ይዞ ይንቀሳቀሳል፡፡ እነርሱም፡-

- በወጣቱ ዙሪያ የሚሰሩ አካላትን አቅም ማጠናከር፣
- በኘሮግራሙ ላይ ወላጆችና ማህበረሰቡ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ወጣቶች ስለራሳቸው እንዲገልጹ እድል መስጠት፣
- ተጋላጭ በሆኑ ወጣቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት ካለባቸው ችግር ማላቀቅ፣
- አጋዥ በማጣት ትምህርታቸውን በማቋረጥ ያለ እድሜ ጋብቻ እንዳይዙ የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፣
- አሣታፊ በሆነ መንገድ የወጣቶችን ችግር ለመቅረፍ መንቀሳቀስ፣
- ተጋላጭ ወጣቶች ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በመቀጠልም በዚህ ኘሮግራም የተፈፀሙ ተግባራትን አንድ ባንድ ዘርዝረው ከነዚህ ተግባራትም የተገኘውን ውጤት /major outcomes/ የሆኑትንም ነጥቦች ለተሳታፊው ግልጽ በሆነ መንገድ አቅርበዋል፡፡

አቶ ያየህ አዲስ፡- የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ

አቅራቢውን አቶ አዳሙ ዳኜውን አመስግነው በቀረበው የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ቤቱ ያለውን አስተያየትና ጥያቄ እንዲያቀርብ በጋበዙት መሠረት፡-

## አቶ ሰለሞን ገላው፡- ከአብክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ

የቀረበው ሪፖርት ጥሩ ነው፤ የተከናወነው ተግባርም የሚያበረታታ ነው፡፡ ለእናቶችና ለወጣቶች ሞት መቀነስ የተያዘውን የሚሊኒየም ግብ ለማሳካት የሚያስችሉ እንደ "ሮድ ማፕ" የሚያገለግል ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ወጣቱ ስለመብቱ እንዲታገል የሚያስችል ፕሮግራም ነው ለማለት እፈልጋለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል ያሉንንም ጥያቄዎች አቀርባለሁ፡፡

- ይህ ፕሮግራም መቼ ተጀመረ? እንዴት ተጀመረ? አሁንስ የት ደርሷል? የሚለውን በግልጽ የሚያሳይ አቀራረብ አይደለም ለምን ይህ አቀራረብ ተመረጠ?
- በዚህ አፈፃፀም ላይ "የስቴክ ሆልደሮች" ድርሻ ጉልቶ አልታየም ይህንን አጉልቶ ማሳየት ለምን አልተቻለም፡፡ እነዚህ አካላት እንደ ስልጠና በመሳሰሉት ተግባራት ድርሻ የላቸውም ወይ?

## አቶ ፈጠነ፡- ከኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን

- አቀራረቡ መረጃን መሠረት ያደረገና የተሰራውን ሥራ በትክክል ያመላከተ በመሆኑ አቅራቢውን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ ይህን ካልሁ በኋላ ጥያቄዎችን አቀርባለሁ፡፡
- ጥሩ ጥሩ ተሞክሮዎች ቀርበዋል፡፡ አቀራረቡም እያንዳንዱ ወረዳ የፈፀመውን ክንውን ነው፡፡ ነገር ግን የተሞክሮው ንጽጽሩ በምን መንገድ ታይቶ ነው ቢገለፅ?
- የማስፋት ጉዳይን በተመለከተ ያልተካተቱ ወረዳዎች አሉ፡፡ ወደፊት እነዚህን ለማካተት ምን ተይዟል ቢገለፁ

## ስማቸውን ያልገለጹ ተሣታፊ ያቀረቡት ጥያቄ

- ይህ ሲምፖዚየም ተዘጋጅቶ በጉዳዩ ላይ እንድንነጋገር መደረጉ የሚያበረታታ ነው፡፡ ለዚህም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡
- በሪፖርቱ ላይ ለበርካታ ወጣቶች የአሰልጣኞች ስልጠና፣ የአመቻቾች እንዲሁም የአቻ ላቻ ስልጠና መሰጠቱ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን ለምን ያህል ወጣቶች ስልጠናው ተሰጠ? ከስልጠና በኋላ የነበረው ክትትልስ ምን ይመስል ነበር? እንዴትስ ተከታተላችሁት የሚለው ነገር ቢገለጽ?

- በኘሮግራሙ ሂደት ላይ ከጊዜ ጊዜ ውጤቱ እየጨመረ መምጣቱ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን እንዴት ጨመረ? ከየት ተነስቶ የት ደረሰ? ምን ያህልስ ጨመረ የሚሉት ጉዳዮች በግልጽ አልታዩም ቢብራሩ?
- ለወጣቱ ምቹ የሆኑ የውይይት አካባቢዎች ተፈጥረውለት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስና በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ እንዲነጋገሩ ተደርጓል ይላል ሪፖርቱ እነዚህ ምቹ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው ቢገለጹ?
- የጤና ባለሙያው ኘሮግራሙን ትኩረት ሰጥቶ የመደገፍ፣ የመከታተል እንዲሁም አገልግሎት የመስጠቱ ሁኔታ ምን ያህል አስተማማኝ ነው?
- ይህ ኘሮግራም ሲፈፀም ያሉ ጠንካራ ጐኖች እንዲሁም ድክመቶች፤ የነበሩ ምቹ ሁኔታዎች ምን ይመስሉ ነበር ለምን አልቀረቡም?

<u>አቶ ሰይድ አሊ፡- ከተቀናጀ የቤተሰብ ኘሮግራም</u>

- በዚህ ኘሮግራም የምንሰራቸው ሥራዎች የመንግስትን ፖሊሲና ስትራቴጅ እንዲሁም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርም ባወጣው ፖሊሲ መሠረት ነው? ይህን በትክክል ፈትሸነዋል ወይ? ኘሮግራሙ ወደፊት ቀጣይ ነው? አሁን ያለንን ተሞክሮ ታች ድረስ በማውረድ የመፈፀማችን ሁኔታ ምን ያህል ነው? የቁርጠኝነት ጉዳይ አሳሳቢ መስሎ ስለተሰማኝ?
- በየጤና ጽ/ቤቱና ተቋማቱ የእናቶችና ወጣቶችን የስነ-ተዋልዶና ጤና ጉዳይ የሚመለከት አካል አለ፡፡ ነገር ግን ሥራው በደንብ አይታወቅም፡፡ ስለዚህ የነዚህን አካላት አቅም ለማጠናከር ወደፊት ምን እቅድ ተይዟል?
- በዚህ ኘሮግራሙ እንዲታቀፍ የተመረጡት ሰባት የወረዳና የከተማ አስተዳደሮች በምን መስፈርት ተመረጡ? ማወዳደሪያው ምንድን ነው?
- በዩኒቨርስቲዎች ላይ የሚሰሩ ሌሎች ተቋማት አሉ፡፡ ተግባሩ እንዳይደጋገም ሁኔታውን በጋራ አይታችሁታል ወይ?

<u>አቶ ያየህ አዲስ፡- የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ</u>

- የቀረቡ ጥያቄዎች በጣም ገንቢና ወደፊት ሥራዎችን እንዴት መምራት እንዳለብን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ ያለባቸው ይህ ኘሮግራም የተዘረጋባቸው ወረዳዎች ይሆናሉ፡፡ ሥለዚህ በዚህ ኘሮግራም

ተጠቃሚ የነበራችሁ ወረዳዎች ሥራውን እንዴት መራችሁት? አስተያየታችሁን ጨምራችሁ ምላሽ እንድትሰጡ እድሉን እሰጣለሁ ባሉት መሠረት፡-

<u>አቶ እሸቱ ካሤ፡- የደራ ወረዳ አስተዳዳሪ</u>

- የእኛ ወረዳ ከተመረጡ ሰባት ወረዳዎች አንዱና በፕሮግራሙ ተጠቃሚ ነው፡፡ ስለዚህ በወዳችን የተሰሩ ሥራዎችን አጭር ምላሽ እሰጥባቸዋለሁ፡፡
- ይህ ፕሮግራም ወደ ወረዳችን ከገባ ጀምሮ በርካታ ተጨባጭ ለውጦችን አግኝተናል፡፡ ወረዳችን ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ፕሮግራም ተጠቃሚ አልነበረም፡፡ ፕሮግራሙንም የመራነው ለተግባሩ ፈፃሚ አካላትን በመለየት ነበር፡፡ በዚህም የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት፣ የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እንዲሁም የትምህርት ጽ/ቤቶች በጋራ እቅድ እንዲያቅዱ በማድረግ በባለቤትነት ይዘው እንዲመሩት በማድረግ ነው፡፡
- ፕሮጀክቱ ብዙ ክፍሎች ያሉትና በርካታ ፕሮግራሞችን ያቀፈ ነው፡፡ ይህንንም ፕሮግራም ገጠር ቀበሌዎች ድረስ በመውረድ የማህበረሰብ ውይይት እንዲደረግ ሁኔታዎች በመመቻቸታቸው በርካታ ለውጦች ተገኝተዋል፡፡ በዚህም ወደ 28,900 የሚደርስ የማህበረሰብ ክፍል የምክርና የደም ምርመራ አግልግሎት አግኝቷል፡፡
- ይህ ፕሮግራም የወጣቶችን ችግር በማወቅ አቅማቸውን እንድንጠቀም አድርጎናል፡፡ ከዚህ በፊት በተለያየ ምክንያት ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወጣቶችም ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ አድርገናል፡፡
- በፊስቱላ ችግር የተጐዱ ሴት ህፃናት ባህሉ ባሣደረባቸው ተጽንኦ ምክንያት ተገልለው ጓዳ ውስጥ እንዲቀመጡ መደረጉ ቀርቶ ወደ ህክምና እንዲመጡ በር እየከፈተ ነው ያለው፡፡ ይህንን ችግር የሚያስከትለውንም ጉዳይ ከስሩ ለመንቀል በወላጆች ላይ ግንዛቤ እየፈጠረ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ፕሮጀክቱ ወደ ወረዳችን ከገባ ጀምሮ በተጨባጭ ለውጥ እየመጣ መሆኑን ገምግመን አረጋግጠናል፡፡

አቶ ጥላዬ ግዛቸው፡- ከማህበረ ህይወት

- በዚህ ጥምረት ኘሮግራም የእኛ ድርጅት ጐንደር ከተማ ላይ ከአቅድ ጀምሮ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ ዩኒቨርስቲው ላይ ይህ ኘሮግራም አለ፡፡ ነገር ግን ችግሩን ሙሉ በሙሉ የሚቀርፍ አይደለም ካለው አቅም አንፃር፡፡ ሥለዚህ ሌሎችም አጋር አካላት ቢገቡበት፡፡
- ድርጅታችን ከፖስፋይንደር ባገኘው ድጋፍ ዳባት ወረዳ ላይ በወጣቶች ስነ-ተዋልዶና ጤና ላይ ሰርተናል፡፡ ይህን ተሞክሮ ይዘን ነው ወደ ጐንደር ዩኒቨርስቲ የገባነው በዚህ ኘሮግራምም በርካታ ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርገናል፡፡ ውጤታማም ሆነናል ማለት ይቻላል፡፡

አቶ ስንታየሁ ዘለቀ፡- ከባህርዳር ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት

የባህርዳር ከተማ አስተዳደር ይህን ኘሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ ሲጀምር የተነሳው ካሉን ገጠር ቀበሌዎች ነው፡፡ እነዚህን ቀበሌዎችም በኘሮግራሙ ላይ ማሣሳተፋችን አበረታች ውጤት አግኝተናል፡፡

- ወደፊትም ኘሮግራሙን በመሉ አቅም ለመፈፀም ማስተባበሪያ ጽ/ቤቱ ከፈፃሚ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ ይህንን ኘሮግራምም ፈፃሚዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉት የበጀት መልቀቂያው ጊዜው በተመቻቸ ሁኔታ ቢኖርና ሰፋ ያለ ጊዜ ቢሰጠው ጥሩ ነው፡፡

ከኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ጤና ጽ/ቤት ሴት ተሣታፊ

- ኘሮጀክቱ ወደ ከተማ አስተዳደራችን እንደመጣ እንዴትና በምን መንገድ ብንሰራ ውጤታማ ልንሆን እንችላለን ብለን ነው አቅጣጫ የመረጥነው፡፡ በዚህ አካሄድም ውጤታማ ሆነናል፡፡
- በከተማ አስተዳደሩ ሥር አምስት የከተማ ስድስት የገጠር ቀበሌዎች አሉን፡፡ በእነዚህ ቀበሌዎቻችን ኘሮግራሙ በብቃት እየተፈፀመ ይገኛል፡፡ ሥለዚህ ሥራው በቅንጅት እየተሰራ ነው፡፡
- ወጣቱ በስነ-ተዋልዶና ጤና ዙሪያ በቂ መረጃ እንዲያገኝና ራሱን ከበሽታ እንዲከላከል ለማድረግም የመረጃ ማዕከል በመክፈት ባለሙያ በመቅጠር አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን፡፡

**አቶ አዳሙ ዳኜው፡- የጥምር ኘሮግራሙ ኦፊሰርና ሪፖርት አቅራቢ ለቀረቡ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ**

- በዚህ ኘሮግራም "የስቴክ ሆልደርስ" ድርሻ በጣም የጐላ ነው፡፡ ይህንንም በመግቢያ ላይ ከራሳቸው አንደበት የሰማነው ስለሆነ እኔ ምንም አልጨምርም፡፡
- ሥራችንን ስንጀምር በሁሉም ዘርፍ ለመነሻ የሚሆኑ ቁጥሮች ነበሩን፡፡ ነገር ግን እዚህ ላይ አላቀረብናቸውም ጥናት ባይደረገም የሚከናወኑ ተግባራት በየዓመቱ መረጃዎች ይኖሩናል፡፡
- ሥራው ሲሰራ ችግር ነበረ፤ ይህም ለፈፃሚው አዲስ ስለነበር ብዥታ ፈጥሮብን ነበር፡፡ ነገር ግን ይህንን በዝርዝር ማቅረብ አልፈለግንም፡፡ ችግሩን ወዲያው መፍታት ስለተቻለ፡፡
- የወጣቶች የስነ-ተዋልዶና ጤና የአቻ ላቻ አገልግሎት ኘሮግራም በአሁኑ ሠዓት በጥሩ ሁኔታ ላይ ነው ያለው፡፡ ለአገልግሎት መስጫ የሚሆን አስፈላጊው ግብዓት እየተሟላላቸው ይገኛል፡፡
- በኘሮግራሙ ላይ የባለሙያዎች ተነሳሽነት ጥሩ ነው፡፡ ይህንንም በመስክ ባደረግነው ጉብኝት አረጋግጠናል፡፡
- በክልል ደረጃ የሚሰጠው የአሰልጣኞች ስልጠና ነው፡፡ ይህ ሥልጠና ከተሰጠ በኂላ ወረዳ ላይ በሚሰጠው የፈፃሚዎች ሥልጠና ወደ ተግባር በመግባት በቀጥታ ሥራውን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ በዞን ደረጃም የሪፖርት ግንኙነት አለ፡፡
- በዚህ ኘሮግራም የታቀፉ ሰባት ወረዳዎችን ስንመርጥ መነሻ ያደረግነው በዩኒሴፍ ያልተያዙ መሆናቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ የምርጫ ሂደትም የዞን አመራሮች ተሣትፈውበታል፡፡ በማለት ምላሻቸውን አጠናቀዋል፡፡

**አቶ እሸቴ ግርማ፡- የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ የሰጡት ምላሽ**

- የቀረቡ አስተያየቶች ለኘሮግራሙ መቃናት ገንቢ ስለሆኑ እንዳለ እንወስዳቸዋለን፡፡ በዚህ መሠረት ለቀጣይ የቀሩ ነገሮችን አስተካክለን እንቀጥላለን፡፡
- ፈፃሚ አካላት ኘሮግራሙን በባለቤትነት እየመሩት እንደሆነ ከደራ ወረዳ አስተዳዳሪና ከኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ የቀረቡ አስተያየቶች አብነት ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

- ከቀረቡ ጥያቄዎች አንዳንዶቹ በጥናት የሚመለሱ ናቸው፡፡ እነዚህን ወደፊት በማጥናት ምላሽ የምንሰጥበት ይሆናል፡፡
- የኘሮግራሙን የልምድ ልውውጥ እንዲሁም የማስፋት ሁኔታ በአስፈፃሚ አካሉ የሚወሰን ነው የሚሆነው፡፡ አሁንም በሚቀርቡት የፎቶግራፍ ኤግዚቢሽን ልምድ መውሰድ የሚቻልበት ሁኔታ ስላለ ይህንን በኘሮግራም የምናየው ይሆናል፡፡
- አብዛኛው የሀብረተሰብ ክፍል ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተጋላጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይበልጥ ተጋላጭ የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል በመለየት ቶሎ ቀድሞ መድረስ አስፈላጊ በመሆኑ በወጣቶች ላይ ትኩረት ሰጥተን ለመስራት ተገደናል፡፡
- ከወጣቶች ጋር በተያያዘ የሚወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን ተግባራዊ ለማድረግና የመንግስትን አቅጣጫ ከግብ ለማድረስ ከወጣቶችና ስፖርትና ከጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር በመሆን በቅንጅት እንሰራለን፡፡ ባለሙያዎችም ፖሊሲውንና ስትራቴጅውን እንዲያውቁ እናደርጋለን፡፡
- ከ2003-2007 ድረስ ባለው የስትራቴጅክ ዘመን “ሮድ ማፕ” ተዘጋጅቶ የት መድረስ እንዳለብን የተቀመጠ አቅጣጫ አለ፡፡ ሥለዚህ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈፀም በሚለው ላይ ጥናት ተጠንቶ ተይዟል፡፡ ይህንን ተግባራዊ በማድረግ ከአምስት ዓመት በኂላ አሁን ያለውን 26.6% ወደ 19.5% ዝቅ የማድረግ እቅድ ይዘናል፡፡ ለዚህም ትምህርት ቤቶች ላይ ጠንክረን መስራት ይጠበቅብናል፡፡
- ከበጀት አጠቃቀም ላይ ሰፊ ችግር ነበረብን፡፡ ገንዘቡ እንደመጣ ቶሎ ወደ ወረዳ የማድረስና ወረዳዎችም ከተጠቀሙ በኂላ የማወራረድ፡፡ ስለዚህ ሁላችንም ያለብንን ችግር በመቅረፍ ሥራዎችን መስራት ይጠበቅብናል፡፡
- ከጤና ጥበቃ ቢሮ እስከ ጤና ኬላ ድረስ አብሮ የመስራትና የትብብር መንፈሱ ጥሩ ነው፡፡ ወደፊትም ይህንን ትብብር በተሻለ ጥረት በማገዝ እንሰራለን፡፡ በቀጣይ ሁላችንንም የሚያረካ ሥራ እንደምንሰራ ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡

<u>አቶ ያየህ አዲስ፡- የሰጡት የማጠቃለያ ሃሣብ</u>

- ይህ ኘሮግራም ሲጀመር ከሃገሪቱ የአምስት ዓመት ዕቅድ ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ ነው የሚታሰበው፡፡ ሥለዚህ ታስቦበት የታቀደ መሆኑን ማየት አለብን፡፡

በመሆኑም በእውቀት ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ ኖሮን ሥራውን ልንመራው ይገባል፡፡

- ለድጋፍ የመጣውን ገንዘብ "ከመሚጨቅ" ወጥተን ለውጥ በሚያመጣ መንገድ አቅደን መሥራት አለብን፡፡ ሥለዚህ ለወጣቱ የሚሰውጠን ሥነ-ተዋልዶና የጤና አገልግሎት አገልግሎት ተቀባዩ ባለበት ሄደን ልንሰጠው ይገባል፡፡ ለዚህም የተደራጁ ወጣቶችን በመጠቀም ትንሽ ሰርተን ብዙ ውጤት ለማምጣት ትኩረት ሰጥተን መስራት አለብን፡፡
- ገንዘብ እንዲመጣልን በጠየቅነው አግባብ ተጠቅመን ለማወራረድ ችግር አለብን፡፡ ሂሣብ ለማወራረድ የምናደርገው ጥረታችንም አነሳ ነው፡፡ ሥለዚህ ያለውን ጥልፍልፍ ችግር መፍታት ፈጥነን ማወራረድ አለብን፡፡ በማለት ሃሣባቸውን አጠቃለዋል፡፡

**ከዚህ በመቀጠል የኤግዚቢሽን ኘሮግራም በተጋባዥ አጋር አካላት ቀርቧል**

በዚህ የፎቶ ኤግዚቢሽን ምልከታ ሥራዎቻቸውን ያቀረቡ በኘሮጀክቱ ታቅፈው ከነበሩ ወረዳዎችና በሌሎች አጋር አካላት የተሰሩ ሥራዎች ሲሆኑ በዚህም በስራው ተሣታፊ የነበሩ ወጣት የክበብ አባላት ለታዳሚው ገለፃ አድርገዋል፡፡ አጋር አካለትም በበራሪ ወረቀቶች፣ በመጽሄቶችና ቡረሸሮችና ጋዜጦች ዓላማቸውንና እንቅስቃሴያቸውን ለተሰብሳቢው አስተዋውቀዋል፡፡

## አጀንዳ 3፡- <u>የፖናል ውይይት በሚቀርቡ የውይይት መነሻ ሃሣቦች ላይ</u>

<u>አቶ ያየህ አዲስ የአብክመ ወጣቶች ስፖርት ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ</u> የዚህን የፖናል ውይይት የሚያቀርቡ ሰዎችን ካስተዋወቁ በኂላ አቶ መሉሰው ልጃለም ከጤና ቢሮ አኳያ የኘሮግራሙን ምንነትና አስፈላጊነት እንዲገልጽ በጋበዟቸው መሠረት ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም ገለፃቸው ወጣት የምንለው ከ10-24 ዓመት ድረስ ያለውን ሲሆን ይህ ክፍልም አስፈላጊ የሆነ የጤና አገልግሎት ያስፈልገዋል፡፡ ለዚህ ነው የሚመለከታቸው አካላት የወጣቶች ሥነ-ተዋልዶ ጤና በሚል ኘሮግራም ተቀርጾ ተግባራዊ እሆነ ያለው፡፡ ሥለዚህ የወጣቱን የጤና ችግር የሚፈታ አገልግሎት እያገኙ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ እንቅስቃሴ አቅም በፈቀደ መጠን የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት በአቅራቢያቸው እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል፡፡ አያይዘውም የስትራቴጅው ዋና ዋና ግቦችን ዘርዝረዋል፡፡

- አገሪቱ በጤናው ዘርፍ የምታሳካውን የምተ ዓመት ግብ መደገፍ፣
- የድህነት ቅነሣ መርሃ ግብርን ማገዝ፣
- በወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ለመፍታት የሴክተሮችን ተሣትፎ ማጠናከር መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

  የስትራቴጅው ራዕይም፡- ማህበራዊ አገልግሎት ለወጣቱ እንዲደርስ በማድረግ ወጣቱ በአገሪቱ ጉዳይ ላይ ተሣትፎ እንዲያደርግ ማስቻል መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

<u>አቶ ያየህ አዲስ፡- የፓናል ውይይት አቅራቢዎችን ተራ በተራ ጋብዘዋል</u>

- አቶ አገኘሁ ገበየሁ የመጀመሪያው ጽሑፍ አቅራቢ የጽሑፋቸው መነሻ ሃሣብ ያደረጉት የአፍላ ወጣትነት እድሜ ምንድን ነው? ምንስ መስራት አለብን? የሚለውን መሠረታዊ ሃሣብ ነው፡፡ አያይዘውም ይህ ነገ አገር በሚረከብ ወጣት ላይ መስራት የሚገባው ነገር ቀድሞ ካልተሰራ የሚገጥመው እጣ ፈንታ አስቸጋሪ ይሆናል ካሉ በኋላ ሃሣባቸውን ሲያጠናክሩ አገራችን የፖሊሲና ስትራቴጅ ችግር የባትም፡፡ ነገር ግን በዚህ በወጣቱ ክፍል ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ አንገብጋቢ ስለሆነ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ የምንሰራው ሥራም በትክክል ወጣቱ ላይ ትኩረት የሰጠና ከጥፋት የሚታደረግ ነው ወይ? የሚለውን ማየት ይጠይቃል ካሉ በኋላ 25% የሚሆነው ህገ-ወጥ ውርጃ እድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች በሆኑ ወጣቶች ላይ የሚከሰት ሲሆን 32% የሚሆነው የእናቶች ሞት የሚከሰተው ደግሞ ህገ-ወጥ በሆነ ውርጃ መሆኑን ጠቁመው እዚህ ላይ ትኩረት ሰጥተን መስራት ይጠይቀናል በማለት ሃሣባቸውን ያጠቃለሉት በየአካባቢያችን ያለውን የወጣቶች ችግር ለመፍታት ምን እየሰራን ነው? የሚለውን ጥያቄ ለተሣታፊው በመጠየቅ ነበር፡፡

<u>ዶ/ር ያለው እንግዳወቅ : - ከባህርዳር ዩኒቨርስቲ ሁለተኛው ጽሑፍ አቅራቢ</u>

- የጽሑፋቸው ጭብጥ የሚያጠነጥነው በወጣቶች የስነ-ልቦና ባህሪይ ላይ ነው፡፡ በዚህም እድገታዊ ስነ-ልቦናን በወጣትነት ስንመለከተው አምስት ብያኔዎች አሉት፡፡ እነርሱም ህጋዊ ብያኔ፣ ማህበራዊ ብያኔ፣ ስነ-ልቦናዊ ብያኔ፣ አካላዊ ብያኔና ሙያዊ ብያኔ በማለት ሙህራን ይከፍሏቸዋል ካሉ በኋላ ስለ አንዳንዳቸው

ብያኔዎች በዝርዝር ገልፀዋል፡፡ አያይዘውም የስነ-ልቦና ተመራማሪዎች ወጣትነትን እንደሚከተለው እየከፈሉ እንደሚጠቀሙበት ገልፀዋል፡፡ እነርሱም ከ13-14 ዓመት የእድሜ ክልል የመባለቂያ፣ ከ15-18 ዓመት ደግሞ የወጣትነት እድሜ ክልል በማለት ሲበይኗቸው በአጠቃላይ ወጣትነት በህይወታችን ውስጥ የምንኖራቸውን ኑሮዎች የምናሳካበት የእድሜ ድልድይ ነው፡፡ ሥለዚህ ወጣቶች ወደ ጉልማሳነት ሲሸጋገሩ ድልድዩ እንዳይሰበር የሚያደርጉ ነገሮች ምንድን ናቸው የሚለውን ማሰብ አለብን ብለዋል፡፡ አያይዘውም ለድልድዩ መሰበር ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ዘርዝረዋል፡፡ እነርሱም ፡-

- ✓ ቀድሞ የወሲብ ድርጊት መፈፀም
- ✓ ባህሪያዊ ሁኔታዎች
- ✓ የማወቅ ጉጉት
- ✓ የህይወት ገጠመኝ
- ✓ የሚዲያ ተጽንኦ /ኢንተርኔት/ መሆናቸውን ዘርዝረዋል፡፡

በመቀጠልም በወጣቶች ስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ ተጽንኦ የሚያሣድሩ ነገሮችን ዘርዝረዋል፡፡ እነሱንም ሲገልጹ ተገቢውን መረጃ አለማግኘት፣ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ለሚ ያጋልጡ ነገሮች ትኩረት አለመስጠት፣ ማህበረሰቡ ግልጽ ሆኖ አለመገኘት፣ ቤተሰብ ለልጆቻቸው በወሲብ ላይ ያለውን ተግባር አለመግለጽና የተለያዩ እፆችንና ሱስ አስያዥ ነገሮችን መጠቀም መሆናቸውን ዘርዝረዋል፡፡

በመጨረሻም የምክር አገልግሎት የሚባለው ምንድን ነው? በትክክል ሙያው የሚያሟላውን ነገር አሟልተን ነው አገልግሎቱን እየሰጠን ያለነው? ኮንዶም ከመጠቀሚያነቱ ባለፈ ወሲብ ፈፃሚዎችንስ ወደ ድርጊቱ እንዲገፋፉ አያበረታታም ወይ? እስኪ በተቃራኒው እንየው? የሚለውን ጉዳዬች የሚያጠያይቁ ስለሆኑ ቤቱ እንዲነጋገርበት ጥያቄ ባዘለ አስተያየት ሃሣባቸውን ሰንዝረው አጠቃለዋል፡፡

<u>ዶ/ር በለጠ ታፈሰ፡- ከአይቴክ ኢትዮጵያ</u>

የጽሑፋቸው መነሻ ነጥብ ያደረጉት በወጣቶች ላይ የአባላዘር በሽታና አስከፊ ሁኔታዎች የሚለውን ሲሆን ይህንንም ለማቅረብ የፈለግሁት አሉ አቅራቢው ለዚህ በሽታ የሚያጋልጧቸው ምን ምን ሁኔታዎች ናቸው የሚለውን መሠረታዊ ሃሣብ ለመዳሰስ በዓለም

ላይ ግማሽ ሚሉዮን የሚሆኑ ወጣቶች በቀን ለዚህ በሽታ ሰለባ እንደሚሆኑ ጠቁመው ከዚህም ውስጥ ከ20-24 ዓመት የእድሜ ክልል ያሉት ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚወስዱ ጠቁመዋል፡፡ ለበሽታው መስፋፋት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችንም አንድ በአንድ በመዘርዘር ለተሣታፊው አስገንዝበዋል፡፡

በበሽታው የተያዙ ወጣቶች ከማህበራዊ ህይወት አኳያ የ ሚደርስባቸውንም ሲዘረዘሩ በወቅቱ ወደ ትምህርት ቤት አለመሄድ፣ በጊዜ ወደ ስራ አለመግባት እንዲሁም የጓደኛ ማጣትና የመሳሰሉት ችግሮች እንደሚገጥማቸው አስታውሰዋል፡፡

ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አኳያ ያለውን ችግር ሲገመግሙ በዓለም ላይ 34 ሚሊዮን ህዝብ ቫይረሱ በደሙ እንዳለበት ሲገመት 11.8% የሚሆነው ደግሞ ከ11-24 የእድሜ ክልል ያለው ወጣት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በአገራችን የቫይረሱ ስርጭት 2.4% በክልላችንም ደግሞ 2.9% የደረሰ መሆኑን በቅርብ የተጠኑ ጥናቶች ማረጋገጣቸውንና የችግሩን አስከፊነት በመረዳት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል የሚለውን ጥያቄ ለተሰብሳቢው በማንሣት የራሳቸውንም ሃሣብ በመዘርዘር ሃሣባቸውን አጠቃለዋል፡፡ እነርሱም፡-

- አመች ሁኔታዎችን መፍጠር /የፖለቲካና ማህበራዊ አካባቢን ማመቻቸት
- ጥሩ ያልሆኑ ጐጅ ልማዶችን ማስወገድ /ቅድመ ጋብቻ ወሲብ፣ የሴት ልጅ ፍልሰትና ግርዛት/
- መረጃዎችን በሰፊው ለወጣቱ ማድረስ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

<u>አቶ ሲሳይ መለሰ፡- የመጨረሻው ጽሑፍ አቅራቢ</u>

ለውይይት መነሻ እንዲሆናቸው ያቀረቡት ርዕሰ ጉዳይ የስነ-ተዋልዶ ጤና ፍላጐት በወጣቶች ምን ይመስላል የሚል ነበር፡፡ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ መሠረት አድርገው ሲያብራሩ ወጣቱ የስነ-ተዋልዶ ጤና ፍላጐቱ አናሣ መሆኑን ጠቁመው የችግሩ መነሻ የሆኑ ጉዳዬችንም አንድ በአንድ አስቀምጠዋል፡፡

በመጨረሻም የወጣቶች የጤና ፍላጐት በአብዛኛው ያልተሟላ መሆኑን ጠቁመው ፍላጐታቸውን መሠረት በማድረግ በክህሎት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በቂ ጊዜና ቦታ ለአገልግሎት መስጫ በማፈላለግ አገልግሎት መስጠት ከእኛ የሚጠበቅ ነው በማለት ጠቁመዋል፡፡ ለዚህም የጤና ባለሙያው በቂና ልዩ የሆነ ስልጠና ያስፈልገዋል፤ ከዚህ ሌላም በኘሮግራሙ አጀማመር

ላይ ወጣቱን በማወያየት ለጉዳዩ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ይገባል በማለት ሃሣባቸውን አጠቃለዋል፡፡

አቶ ያየህ አዲስ፡- አራቱንም ጽሑፍ አቅራቢዎች አመስግነው የቀረቡትን የመወያያ መነሻ ነጥቦች መሠረት በማድረግ ከእኛ አንፃር እንዴት እናየዋለን ይህንን ኘሮግራም የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ እንድንችል የሚረዱ ሃሣቦች ግልጽ ባልሆኑት ላይ ጥያቄዎች ማቅረብ ይቻላል ብለው ለቤቱ በሰጡት እድል መሠረት፡-

<u>አቶ ሰለሞን ገላው፡- ከአበክመ ጤና ጥበቃ ቢሮ</u>

- ውይይት ያቀረቡትን ሰዎች በሙሉ ማመስገን እፈልጋለሁ የተሰጠን ትንተና ሙያዊ በመሆኑ ወደፊት ሥራ መስራት የምንችልበት ትጥቅ በመያዝ ቅድመ ዝግጅት አድርገናል ማለት ይቻላል፡፡
- የወጣትነት ሁኔታ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ ሥለዚህ ወጣቶች ወደፊት በሚመሩት ይህወት ተግባራዊ እንዲያደርጉት እኛ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት አለብን፡፡
- በወጣቱ ዙሪያ ሊያሰራ የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጅ አለን፤ ይህም አገልግሎቱንና መረጃውን ለተጠቃሚው በተገቢው መንገድ ማድረስ የሚያስችል አቅጣጫ ያለው ነው፡፡ ሥለዚህ ለተግባራዊነቱ ሰፊ ሁኔታ ይጠበቅብናል፡፡
- ይህንን ኘሮግራም ውጤታማ ለማደረግ ማህበረሰቡ ዘንድ መድረስ ይጠበቅብናል፡፡ ቀበሌ ላይ የመምህራንና የሴቶች ማህበራት አሉ ሥለዚህ ይህንን ሲስተም ተጠቅመን መስራት ብንችል ምን አለበት?
- በዚህ ጉዳይ ላይ ተቀናጅቶ መስራት ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ከላይ እስከታች ያለው አካል ወጣቱ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የተቀናጀ ተግባር ማከናወን ይኖርብናል፡፡
- የእኛ ጤና ተቋማት የተሰሩት አዋቂዎች ሲታመሙ የሚታከሙበት እንዲሆን ተደርጕ ነው፡፡ ሥለዚህ ወጣቶች በነፃነት ሄደው ሳይሸማቀቁ የስነ-ተዋልዶና ጤና አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑበት የራሳቸው ማዕከል እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባናል፡፡
- በወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ቢሮ በኩል በየአካባቢው የወጣቶች መዝናኛ ማዕከላት እየተገነቡ ይገኛሉ፡፡ ሥለዚህ በእነዚህ ማዕከላት የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች ቢደረግ ጥሩ ነው የሚል አስተያየት አለኝ፡፡

## አቶ ወንድወሰን አሰፋ፡- ከጐንደር ማህበረ ህይወት

- በክልላችን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አሉ፣ ከዚህ በተጨማሪም ክልላችን የቱሪስት መዳረሻ ነው፡፡ ሥለዚህ በእነዚህ አካላት አማካኝነት የሚመጣውን የቫይረስ ስርጭት ለመግታት እንዲቻል የመረጃ ክፍተቱ ችግር ቢፈታና በቀጥታ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ ቢፈጠር፡፡
- የወጣቶች የስነ-ተዋልዶና ጤና አገልግሎት የሚሰጠው ከሌሎች የጤና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ጋር ተደርቦ ነው፡፡ ይህ ደግሞ አገልግሎቱ ለተፈለገው አካል የመድረስ ችግር እንዳያመጣ የሚለይበት ሁኔታ ቢፈጠር፡፡
- የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ወጣቶች ወደ አገልግሎቱ እንዲመጡ ከማድረግ ይልቅ አገልግሎቱ ወደ እነርሱ ቢሄድ ተደራሽነቱ የተሻለ ይሆናል፡፡ ሥለዚህ በዚህ መንገድ ቢሰራ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአገልግሎት መስጫ ጊዜው መቆራረጥ የለበትም ወጥና ቋሚ በሆነ ጊዜ ቢሰጥ፡፡
- ወላጆቻቸውን በተለያየ ምክንያት ያጡ ህፃናትና ወጣቶችን ድጋፍ ስናደርግ ሌሎች አካላትን ያካተተ መሆን አለበት፡፡ በተለይ ትምህርት ቤቶች በጉዳዩ ላይ እውቅና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባናል፡፡
- ክልላችን የማህበረሰብ ውይይት በማድረግ ተጠቃሽ ነው፡፡ ጥሩ ውጤትም አስመዝግቧል፡፡ ሥለዚህ ይህንን ኘሮግራም አጠናክረን ብንቀጥል፡፡

## አቶ መልሰው የተባሉ ተሣታፊ ያቀረቡት ሃሣብ፡

- ከወጣቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት እስትራቴጅ ተነድፎላቸው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ትኩረታቸውም በወጣቶች ላይ ነው፡፡ ነገር ግን እውቀትና በቂ መረጃ አለመኖሩ ችግሩን በቀላሉ መቅረፍ አላስቻላቸውም ይህ ለምን ሆነ የሚለውን ማየት ይጠበቃል፡፡
- በክልላችን ስለወጣቱ ስነ-ተዋልዶ ጤና ችግርና አገልግሎት አሰጣጥ በግልጽ እንዳንነጋገር የባህል ተጽንኦ አለብን፡፡ ሥለዚህ ቤተሰብን ትኩረት ያደረገ ሥራ መሰራት የለበትም ወይ? ክፍተቱን ለመሙላት እዚህ ላይ ቢሰራ፡፡

አቶ ወንድወሰን፡- ከኮምቦልቻ ከተማ አስተዳደር

- የአቶ ሲሳይ መለሰ ጽሑፍ ያተኮረው አዲስ አበባ ከተማ ላይ በተጠና መረጃ ላይ ነው፡፡ ይህ ከእኛ ክልል ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ጠቃሚነቱ ምን ያህል ነው ይላሉ?
- ዶ/ር ያለው የኮንዶምን ስርጭት ጉዳይ በጥያቄ መልክ አንጠልጥለው ትተውታል በእርሰዎ አስተያየት ምን መሆን አለበት ይላሉ፡ቢገልጹልን?

ስማቸውን ያልጠቀሱ ወንድ የውይይት ተሣታፊ

- በአሁኑ ሠዓት መረጃ የምናስተላልፍበት መንገድና የመልዕክት አሰጣጣችን ጉዳይ ከነበረበት ወጣ ቢል ምን አለበት? እስከ አሁን የተጓዝንበት መንገድስ አዋጭ ነው ወይ?
- በአሁኑ ሠዓት ከዩኒቨርስቲ የሚመረቁ ወጣት ተማሪዎች ዲግሪ ብቻ ሣይሆን ሌሎችን ደባል ሱሶችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ይዘው የሚወጡ ቀላይ አይደሉም፡፡ ሥለዚህ ይህንን የትምህርትና የህይወት ተሞክሮ ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አካፍለዋል ወይ? ዶ/ር ያለው ይህንን ጉዳይ ቢገልጹልኝ

አቶ ያየህ አዲስ፡- በቀረቡት ጥያቄዎች ዙሪያ ጽሑፍ አቅራቢዎች እንደጥያቄው አግባብ እንዲመልስ እድሉን እጣለሁ ባሉመት መሠረት፡-

ዶ/ር ያለው እንዳወቅ ለተጠየቁ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ

- የካውንስሊንግ አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ሰልጥነው አስፈላጊውን አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ ነገር ግን አጥጋቢ ነው ማለት አይቻልም ብለዋል አቶ ሰለሞን ከጤና ቢሮ፡፡ ማማከር ማለት አፍጦ ለመጣው ችግር መፍትሄ ማምጣትና ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንዲመጡ ማድረግ ነው ካሉ በኋላ ሃሣባቸውን ሲያጠናክሩ የማማከር ጉዳይ በአንድ ቀን ወይም በወር የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም ዓመታትን የሚወስድ የማያሰልስ ተግባር መሆኑን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ሌላም የካውንስሊንግ አገልግሎት የሚሰጥ ሰው ሚስጥር ጠባቂ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን ስንቶቻችን ነን የተጠቃሚውን ሚስጥር የምንጠብቀው? በማለት ታዳሚውን ጠይቀዋል፡፡
- ማህበረሰቡ በወጣቱ ላይ እንዲሰራ ብናማክረው ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን እንዴት እናማክረው? ምንስ እናሟላ? የሚለውን ማየት አለብን እንደየፍላጐቱ ችግሩን የምንፈታ ከሆነ ጥሩ ውጤት ላይ መድረስ ይቻላል፡፡ ለዚህም የቁርጠኝነት

ጉዳይም በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አሁን ያለው ኘሮግራም ካበቃ በኋላ ወዴት ነው የምንሄደው እንዴትስ ነው ኘሮግራሙን ማስቀጠል እንችላለን የሚለውን ቆም ብለን ማሰብ አለብን፡፡ አንድ ቀን እርዳታው ሲያቆም ሥራችን እንዳይቋረጥ እሰጋለሁ ብለዋል፡፡

- በስነ-ተዋልዶና ጤና አገልግሎት እንዲሁም ተዛማጅ ጉዳዬች ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት ወደ ወረዳዎች እንልካለን፡፡ ነገር ግን እነዚህ አካላት በባህሪያቸው ብቁ ናቸው ወይ? የሚለውን በጥንቃቄ በየጊዜው መፈተሽና ማረጋገጥ አለብን፡፡
- ብዙ የማህበረሰብ ውይይት በቡና ጠጡ ኘሮግራሞች ይካሄዳሉ፡፡ እስከ አሁንም ሲካሄዱ ቆይተዋል፡፡ ይህ በቡና ጠጡ ዝግጅት ውይይት በማካሄድ ወጣቱን በሙሉ መድረስ እንችላለን ወይ? ከወዲሁ የተለየ አማራጭ መያዝ ይኖርብናል፡፡ አልያ ዘላቂነቱ አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡
- የኮንዶም ሥርጭት ለጥንቃቄ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የስርጭቱ ሁኔታ ወጣቶችን ለወሲብ ፍላጐት ይገፋፉ ይሆን የሚል ስጋት አለብኝ፡፡ ለዚህ ነው ለጉዳዩ አስፈላጊ ጥናት ቢደረግ ያልሁት፡፡
- ወጣቶችን ቤተሰብ ወይም በትምህርት ቤቶች ሊደግፏቸው ይገባል፡፡ ምንም ድጋፍና ምቹ ሁኔታ ሣንፈጥርላቸው ወጣቶችን ስንረግም እንገኛለን፡፡ ሥለዚህ ለወጣቱ ሥነ-ምግባር የተስተካከለ መሆን ምቹ ሁኔታዎችን ልንፈጥርላቸው ይገባል፡፡ ይህም የማህበረሰቡና የመንግሥት ኃላፊነት ነው፡፡
- ያለኝን የህይወት ተሞክሮና እውቀት እንዳካፍል ከተጠየቅሁ ለማካፈል ዝግጁ ነኝ፡፡ ነግር ግን በባህርዳር ዩኒቨርስቲ እንዲህ ዓይነት መድረክ ተፈጥሮ የጋበዘኝ አካል የለም፡፡
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የስርጭት ሁኔታ፣ የመከላከልና ሌሎች ተዛማጅ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት የመረጃ ማስተላለፊያ መንገድ ላይ እኔ ስጋት አለኝ፡፡ በትክክል መልዕክቱ ከልባችን እየተረዳነው ነው ወይ? ይህንን በጥናት በተደገፈ መልኩ መቀየር አስፈላጊ ይሆናል፡፡

<u>ዶ/ር በለጠ ታፈሰ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ</u>

- ኮንዶምን ማን እንደተጠቀመ ለማጥናት በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ የአጠቃቀም መጠኑን የምንለካው በተሰራጨው ቁጥር ነው፡፡ ይህ ደግሞ መጠኑን በትክክል

ለመለካት አስቸጋሪ ነው፡፡ በስርጭት በኩልም ወጣቱ ነፃ ሆኖ በሚያገኝበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይገባል፡፡ ይህንንም እናደርጋለን፡፡

- ወጣቶችን በፕሮግራሞች ላይ ማሣተፍና የአጠቃቀም ደረጃዎችንና አስፈላጊ ሰርቪስ በቅናሽ ዋጋ ማቅረብ ይጠበቃል፡፡ በዚህም ወጣቱ የአቻ ላቻ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይጠቅማል፡፡
- የጤና መልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች መጠናት አለባቸው፡፡ መረጃዎች በአግባቡና ለውጥ ሊያመጡ በሚችሉ መንገድ ወጣቱ ባለበት አካባቢ እንዲደርስ ማድረግ ይጠበቃል፡፡ በማለት ሃሣባቸውን አጠናቀዋል፡፡

## አቶ ሲሣይ መለሰ ለተጠየቁት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ

- የወጣቶችን የአቻ ላቻ አገልግሎት አሰጣጥ ካሉት ተቋማት ጋር አስተሳስሮ መስጠት ይቻላል የሚል አስተሳሰብ ያላቸው አሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለብቻቸው እየተዝናኑ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ይሻላል የሚሉም ወገኖች አሉ፡፡ ሥለዚህ ይህንን ወደፊት እንደ አዋጭነቱ እንዲሄድ በጥናት ቢመለስ ጥሩ ነው፡፡
- ይህ ኘሮግራም እስከመቼ ነው አዋጭ ሆኖ የሚቀጥለው የሚለውን እንደ አካባቢያችን ማህበረሰብ ባህል ጉዳይ ተጠንቶ የሚመለስ ይሆኖል፡፡
- በአቅረብሁት የመወያያ መነሻ ጽሑፍ ላይ የተጠቀምሁት መረጃ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ የተጠና ነው፡፡ ይህም መረጃ በክልላችን ያለውን ችግር ይጋራል የሚል እምነት አለኝ፡፡ እንኳን በአገራችን ላይ የተጠና ቀርቶ በሰብ ስሃራ አገራት የተጠና ጥናትም ቢሆን ተመሣሣይ ነው ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይም በአማራ ክልል ላይ የተጠና ጥናት እስከ አሁን የለም፡፡
- በአብዛኛው ወጣቶች የመጀመሪያ የወሲብ ግንኙነት ሲፈጽሙ ኮንዶም የመጠቀም ችግር አለባቸው፡፡ ሥለዚህ የቅስቀሳ መንገዶች ሊቀይሩ ይገባቸዋል፡፡

## አቶ ሙሉሰው ልጃለም የሰጡት ምላሽና አስተያየት

- የወጣቶች ጤና አገልግሎት አሁን በተሟላ ሁኔታ በየአካባቢው የለም፡፡ ወጣቱም አገልግሎቱን ሲፈልግ አያገኝም፡፡ ሥለዚህ ይህንን እንዴት ማስተካከል ይቻላል? ሁሉም አካላት ሊያስቡበት ይገባል፡፡
- ለወጣቶች የጤና አገልግሎት ለመስጠት ህንፃ መስራት አይጠበቅብንም፡፡ በመሆኑም ድንኳን በመስራት አገልግሎት መስጠት እንችላለን፡፡ ሥለዚህ እኛን

የሚመጥን አገልግሎት መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ ትልቁ ጉዳይ ወጣቱን ካለበት ችግር መታደግ ነው፡፡

- እኛ ጠንካራ ከሆን ወደምንፈልገው አቅጣጫ ወጣቱን መቀየር ይቻላል፡፡ ሥለዚህ እዚህ ላይ ትኩረት ሰጥተን መስራት አለብን፡፡ በእኛ በኩል ሥራውን ከላይ እስከ ታች ለማስተሳሰር የበኩላችንን አስተዋጽኦ እያበረከትን እንገኛለን፡፡

  <u>*አቶ ያየህ አዲስ የሰጡት ማጠቃለያ ሃሣብ፡-*</u> ከቤቱ ጥሩ ሃሣቦች ቀርበዋል፤ ከፓናሊስቶችም አስተማሪ የሆነ ሃሣብ ቀርቧል፡፡ ሥለዚህ ሁላችንም ተቀናጅተን መስራት አለብን፡፡ ሥለዚህ እንደ ክልል እንዲሁም እንደ ሃገር ወጣቱን ማደራጀት ይጠበቃል፡፡ ወጣቱ ከተደራጀ እርስ በርስ ሊማማር ይችላል፡፡ ሌሎችንም ተግባራት መስራት ይቻላል፡፡

- በቀረበው ኤግዚቪሽን በአብዛኛው ሥራዎችን ይገልፁ የነበረው ወጣቶች ናቸው፡፡ ሥለዚህ ወጣቱን ካደራጀነው ብዙ ስራ ሊሰራ ይችላል፡፡ በመሆኑም በማደራጀት ላይ ትኩረት ብንሰጥ፡፡

- ወጣቶች በግል ሲገናኙ የራሳቸውን ችግር አውጥተው ይነጋገራሉ፡፡ በመሆኑም ችግራቸውን መግለጽ የሚችሉበት ቦታ በሰፊው አልተዘጋጀም ይህንን ማስፋት ይጠበቅብናል፡፡

- ሌላው ደግሞ እነርሱ ባሉበት አካባቢ አገልግሎቱን ማድረስ የሚጠበቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

<u>*በሚቀጥለው ቀን ዶክመንታሪ ፊልም ቀርቧል፡፡*</u>

- ፕሮግራሙ በተካሄደባቸው ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች የተከናወኑ ተግባራትን በዶክመንታሪ ፊልም በተደገፈ መረጃ ዲስኘለይ በሆነ መልኩ ለተሳታፊዎች ቀርቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በወረዳና ከተማዎች የተሰሩ ጥሩ ተሞክሮዎች ቀርበዋል፡፡

## አጀንዳ 4፡- <u>የሲምፖዝየሙ ማጠቃለያ ውይይት</u>

<u>*አቶ ያየህ አዲስ፡- የአብክመ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ*</u> አጀንዳውን አስመልክተው ሃሣብ ሰጥተዋል፡፡ ለዚህ ኘሮግራም መቀጠል የተሻለ ስልት ለመጠቀም ምን ማድረግ

አለብን የሚለውን መወያየት ስላለብን ከቤቱ ሃሣብ እንዲሰነዘር ጠይቀዋል፡፡ በዚህ መሠረት ከቤቱ የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

<u>አቶ አበበ፡- ከንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ</u>

- በትናትናውና በዛሬው እለት የቀረቡ ኘሮግራሞች ጥሩ ናቸው፡፡ በቀጣይስ ምን መስራት አለብን በሚለው ላይ ሃሣብ መስጠት እፈልጋለሁ፡፡ በክልሉ ባሉ ትላልቅ ከተሞች ላይ ተጠናክረን ብንሰራ የተሻለ ነገር ማምጣት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ወጣቶች የት ነው ያሉ? እንዴትስ ወደ አገልግሎቱ እናምጣቸው? የሚለውን ሁሉም ወረዳ ማየት አለበት፡፡ ሥለዚህ በትምህርት ቤት ውስጥ ስንት ሠዓት ይቆያሉ? በዩኒቨርስቲስ ምን ያህል ሠዓት ይቆያሉ? የሚዝናኑትስ የት ነው? የሚሉትን ነገሮች በመለየት ስልት ቀይሰን ልንሰራ ይገባል፡፡ የባህዳር ዩኒቨርስቲ ጉዳይ በየአካባቢው የሚነሳ ይመስለኛል በመሆኑም ጥናት በማድረግ ችግሩን መቅረፍ ይገባናል፡፡
- በዩኒቨርስቲዎች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ብቻ ለይቶ ካውንስሊንግ የሚያደርግ ባለሙያ አለን ወይ? ሥለዚህ ከምንም በላይ እዚህ ላይ መስራት የሚገባን ነገር ብንሰራ ጥሩ ነው፡፡
- በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የጋይዳንስና ካውስንሊንግ አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ አሁን ተቋርጦ ከሆነ በስፋት መቀጠል አለበት፡፡ ለዚህም ትምህርት ቢሮ ትኩረት ቢሰጠው፡፡
- የኮብልስቶን ሥራ ላይ ወጣቶች በስፋት ይገኛሉ፡፡ ሥለዚህ በዚህ አካባቢ የምክር አገልግሎት መስጠት እንዲቻል የካውንስሊንግ ኘሮግራም ቢካሄድ፡፡ በተጨማሪም ሥራ መፍጠሪያ ቦታዎች እና ፋብሪካዎች ላይ ኘሮግራሙ ትኩረት ቢያደርግ፡፡
- በንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኘሮግራም መሠረት በዓመቱ ውስጥ አራት መድረኮች ፈጥረን በትላልቅ 50 ከተሞች ላይ ስለኮንዶም አቀራረብ ተነጋግረናል፡፡ በሆቴሎች ላይ የኮንዶምን ስርጭት ምን ይመስላል እንዴት እየቀረበ ነው በሚለው ዙሪያ ውይይት አድርገናል፡፡ በተገቢው መንገድ አገልግሎት የማያቀርብ ሆቴል ሌሎች አገልግሎቶችን እንዳይሰጥ (እንዲዘጋ) የተደረገበት አቅጣጫ ነበር፡፡ ሥለዚህ የከተማ አስተዳደሮችም በየወረዳችሁ ይህንን ተግባር ብትፈጽሙ፡፡

አፈፃፀሙም የእኛን ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ስለሆነ ጠንክረን ብንሰራ ጥሩ ይመስለኛል፡፡

- የጋይዳንስና ካውንስሊንግ ሥራ በፖይለት ደረጃ ብንሰራ፣ የኮንዶም አቅርቦትና አጠቃቀም ላይ ሆቴሎችን መከታተል ይገባል፡፡ ሥለዚህ ወጣቶች ያሉበትን ቦታ ለይተን ተቀናጅተን ብንሰራ የተሻለ ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብለዋል፡፡

<u>ወ/ሮ አመለወርቅ የተባሉ ተሣታፊ ያቀረቡት ሃሣብ</u>

- አሁን ጅምር እንቅስቃሴ አለ፡፡ ነገር ግን ጠንክረን ያልሰራንበት ሁኔታም ይታያል፡፡ ይህን ማስተካከል ይጠይቃል እነዚህ አካላት ለስርጭቱ ተጋላጭ ናቸው፡፡ ሥለዚህ ለወጣቱ የስነ-ተዋልዶና ጤና ትምህርት መሰጠት አለበት፡፡
- ኘሮግራማችንን በየቀበሌው በማውረድ የአቻ ላቻ ወጣቶች በስነ-ተዋልዶ ትምህርት ምንድን ነው የሚለውን ማወቅ እንዲችሉ በጥንቃቄ በተለየ ኘሮግራም መስራት አለብን፡፡
- የወጣቶች መዝናኛ ክበብ በየቀበሌው አልተሰራም፡፡ ሥለዚህ ተከልሎ የተቀመጠው ቦታ ተሰርቶ ለወጣቱ አገልግሎት መስጠት የሚችልበት ሁኔታ ቢፈጠር፡፡ የባህርዳር ሞዴል የወጣት ማዕከሉ ጥሩ አገልግሎት እየሰጠ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ቀበሌዎች ቢወርድ አገልግሎቱን ማስፋት ይቻላል፡፡
- ሰዎች ኮንዶምን ኮንዶም መሆኑን ብቻ ነው የሚያውቁ እንጅ ስለ አጠቃቀሙ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ነው፡፡ ሥለዚህ ግንዛቤ በመስጠቱ ዙሪያም አሁንም መስራት ይጠበቅብናል፡፡

<u>አቶ መኩሪያ ዳኛው፡- ከአማራ ውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን</u>

- ብዙ ጊዜ በስራዎቻችን አካባቢ ጥሩ ያልሆኑ ኃላፊዎች ሳይኖሩ ሲቀሩ የእኛን ኃላፊነት ከመወጣት ይልቅ ወደማይሆን ነገር ውስጥ እንገባለን ይህ መቀረፍ አለበት፡፡
- በየከተሞቻችን ለወጣቶች መዝናኛ እየተባለ የተከለሉ ቦታዎች በአግባቡ ጥቅም ላይ ቢውሉ አሁን ያለምነውን ነገር መስራት እንድንችል ቢደረግ፡፡ ይህም ልጆች ከትምህርት ቤት ውጭ የሚዝናኑበት ሁኔታ ሊመቻች ስለሚችል በአንድ ላይ ተሰብስበው ስለችግሮቻቸው ያወራሉ፡፡

<u>አቶ ሙሉቀን አየሁ፡- ከባህርዳር ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት</u>

- ይህ ኘሮግራም ተግባራዊ ሲደረግ የእኛም ጽ/ቤት ከሃብኮ ጋር በመነጋገር ኘሮጀክት በመቅረጽ ተንቀሳቅሷል፡፡
- በከተማችን ውስጥ ሴተኛ አዳሪዎችን በምግብ ነክ የስራ መስክ በማሰልጠን ወደዚህ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ እንደ እኛ ከተማ የትኩረት መስኮቻችን ተማሪዎችና መምህራን ሊሆኑ ይገባል፡፡ በነዚህ አካላት ላይ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ይጠበቃል፡፡
- በፋብሪካ ሠራተኞችና በእምነት ተቋማት ላይ ትኩረት ሰጥተን መስራት አለበን፡፡
- በወጣቶች ማዕከላት ላይ የካውንስሊንግ ሥራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ሥለዚህ በየከተሞች ይህንን መጀመርና ውጤቱን ማየት አለብን፡፡
- ይህንን ኘሮጀክት ከሰባት ወረዳዎች ውጭ ወደ ሌሎች ወረዳዎች ማስፋት አይቻልም ወይ? አሁን የታየው ለውጥ የመጣው እንደ ክልል ስለሰራን ነው ወይስ በሰባቱ ወረዳዎች ላይ ብቻ ስለተሰራ ነው፡፡ ይህ መፈተሽ አለበት፡፡ ሰባቱ ወረዳዎችስ ከሌሎቹ የተሻልንበትም በምን እንደሆነ ቢታወቅ፡፡

<u>አቶ ሙሉጌታ ካሣይ፡- ከዋግኸምራ ዞን ሃብኮ</u>

- በዩኒቨርስቲዎች ላይ ብቻ መስራት ተገቢ ነው ወይ? መሰረቱ ታች ላይ ነው፡፡ መስራት ያለብን፡፡ ሥለዚህ ከታች መሰረቱን ማስተካከል አለብን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲ ውጭ ክረምት እኛ ላይ ነው የማያሳልፉት ሥለዚህ በተነደፈው የበጐ ፈቃድ አገልግሎት እያሰራናቸው ነው ወይ? የሚለውን ማየት ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ተግባር ያልተራመድነው ሥለሆነ ማየት ይጠበቃል፡፡
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የአባላዛር በሽታ ትልቅ መዘዝ ነው፡፡ ሥለዚህ ይህንን ለመከላከል ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን ማየት አለብን፡፡ ለአባላዛር በሽታ ራሱን የቻለ የመከላከል ስልት ቢቀየስለት በጣም ጥሩ ነው፡፡ ሥለዚህ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፤ ባለቤትም የለውም፡፡
- የሴት ኮንዶም በየዓመቱ እናቅዳለን ነገር ግን አቅርቦቱ የለም፡፡ ሥለዚህ በሌላ ነገር ላይ ለምን ሥልጠና ይሰጣል፡፡ ይህንን ክልሉ ማየት አለበት፡፡

- በሴተኛ አዳሪዎች ላይ ከመስራታችን በፊት ወደ ከተማ ፍልሰቱ ላይ አበክረን /ቀድመን/ መስራት አለብን፡፡ በገጠር ከእርሻ መሬት አሰጣጥ ጀምሮ ማየት አለብን፡፡
- የልጃገረዶች ክበብ በየትምህርት ቤቱ መጠናከር አለበት፡፡ በዚህም ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈፀም ለአደጋ የሚያጋልጥ መሆኑን ማበረታታት አለብን፡፡
- ከማህበረሰብ ውይይት ጋር በተያያዙ በሻይ ቡና ኘሮግራም መካሄዱ ጥሩ አይደለም፡፡ ወደፊት አንድ ወጥ የሆነ ነገር ብንይዝ ጥሩ ይመስለኛል፡፡

## አጀንዳ5፡- <u>በቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዬች</u>

<u>አቶ ያየህ አዲስ፡- መድረኩን ለአቶ እሸቴ ግርማ ሰጥተዋል</u>

<u>አቶ እሸቴ ግርማ፡-</u> በቀጣይ በየደረጃው ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዬችን መሠረት በማድረግ የቀጣይ የትኩረት ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡ እነርሱም፡-

- በየትምህርት ቤቱ የመረጃ ሥርዓቶችን ማጠናከር፡፡ በዚህም ከአጋር አካላት ጋር የስነ-ተዋልዶ ጤና መረጃዎች በቀላሉ መንገድ እንዲደርሳቸው ማድረግ፣
- የሴተኛ አዳሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ እንዲቻል ገጠር ላይ የተጠናከረ ሥራ መስራት፣
- ለህፃናት የህይወት ክህሎት ሥልጠና በመስጠት ኮትኩቶ ማሳደግ፣
- በቴክኒክና ሙያና በግል ኮሌጆችና በኘሪፓራቶሪ ትምህርት ቤቶች ላይ ለመስራት እቅድን መከለስ፣
- የበሽታው ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍልን በጥናት በመመለስ ያለንን ድጋፍ አጠናክረን መቀጠል፣
- የእምነት ተቋማት ከእምነታቸው ባለፈ ውጤት ሊያመጣ በሚችል መልኩ እንዲሰሩ ማድረግ፣ የሐይማኖት አባቶችም ለውጥ ሊያመጡ በሚችል መልኩ ማንቀሳቀስ፣
- ተንቀሳቃሽ የሆነ የምክርና የደም ምርመራ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሥራን አጠናክሮ መቀጠል፣
- የትኛው ቦታ ላይ ምን አገልግሎት መስጠት አለበት የሚለውን በመለየት አገልግሎቱን መስጠት፣

- እያደጉ ባሉ ከተሞችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በስፋት አለባቸው በሚባሉት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፣
- በመንግሥት ሴክተሮች ላይ (በመንግሥት ሠራተኛው ላይ) የምክርና የደም ምርመራ ተግባርን አጠናክረን መስራት፣
- የሴት ኮንዶምን ለማሰራጨት የሚያስችል ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ነገር ግን አቅርቦቱ የለም፡፡ በዚህም ላይ ትኩረት ሰጥተን ሰፊ ሥራ እንሰራለን፣
- በሆቴሎች ላይ በሁሉም መኝታ ቤቶች ላይ የኮንዶም ሥርጭት እንዲደርስ /በየቀኑ/ የማድረግ ሥራ እንሰራለን፣
- የአባላዘር በሽታን በመከላከል የሥልጠና ክፍተት አለ የሚለውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ባለሙያዎች እንዲሰለጥኑ እናደርጋለን፣ ሥልጠናውም ለመንግስትና ለግል ጤና ተቋማት ባለሙያዎች ይሆናል፡፡
- የወጣት ማዕከላት፣ ዩኒቨርስቲና ሌሎች ላይ ከVCT አገልግሎት በተጨማሪ ሌሎችንም ሥልጠናዎች ይሰጣል፡፡ ከዚህ ሌላም ወጣቶች የምክር አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ ከትምህርት ቢሮ ጋር አብሮ መስራት ይጠይቃል፣
- አሁን እየተካሄደ ያለውን የማታ ተማሪዎች የ VCT እና የኮንዶም አቅርቦት ሥራን አጠናክረን እንቀጥላለን፣
- ማህበረሰቡ በራሱ አቅም ገንዘብ በማዋጣት አስፈላጊውን ሥራ እንዲሰራና ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን እንዲደግፉ የግንዛቤ ማሳደግ ሥራ መስራት አለብን፣
- አሰራሮችን ለማስተካከል የሥራ ሂደቱን TO BE እያየን ነው፡፡ በዚህም በጀት ዓመት ወደ ፈፃሚ አካሉ እንለቃለን፡፡ ነገር ግን የሚሰጠውን በጀት ተጠቅሞ በወቅቱ ያላወራረደ አካል አለ እዚህ ላይ የተጠናከረ ሥራ ለመስራት፣ ቦርዱም አቅጣጫ ያስቀምጥበታል፡፡
- የዘንድሮው የሥራ አቅጣጫችን ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ በቂ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይሆናል፡፡ ይህንንም በተሟላና ወቅታዊ መረጃ በማድረስ በኩል ትምህርት ቤቶችን እንጠቀማለን በማለት ሃሣባቸውን አጠቃለዋል፡፡

<u>አቶ ያየህ አዲስ የሰጡት ማጠቃለያ ሃሣብ፡-</u> እንደ ክልሉ መንግስትና እንደ ቦርድ አባልነቴ የተያዘውን አቅጣጫ በመጠቀም ሃሣቡን አጠናክረዋል፡፡ በዚህም፡-

- ዛሬ የVCT አገልግሎት የመስጠት ጉዳይ ተጠናክሮ እየቀጠለ ነው፡፡ በአሁኑ ሠዓት በግልጽ የሚመረመረው ሰው ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡ ሥለዚህ ይህ ያወጣነው እድገት ሥለሆነ እድለኞች ነን፡፡ በመስራታችን የመጣ ውጤት መሆኑንም መገንዘብ አለብን፡፡ ነገር ግን የታደፈነውን ሰደድ ማጥፋት ይጠበቅብናል፡፡
- በወጣቶች ፖሊሲና ስትራቴጅ ውስጥ እንደተካተተው የወጣቶች የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ተመላክቷል፡፡ ሥለዚህ አመራር ላይ ያለን ሰዎች ይህንን ሰነድ በበቂ ሁኔታ ተገንዝበን መግባት ይጠበቅብናል፡፡
- በአሁኑ ሠዓት ወጣቱ ሊፈታለት የሚገቡ በርካታ ጥያቄዎች ይዟል፡፡ ሥለዚህ እኒህን ጥያቄዎች ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ ይህ ካልሆነ አደጋው የከፋ ስለሚሆን የመፍታት ግዴታ አለብን፡፡
- ይህንን ሥራ በምንመራበት ጊዜ ራሣሳችን "ሮል ሞዴል" መሆን አቻል አለብን፡፡ ሞዴልነታችንንም የምናሣየው በሁለንተናዊ እንቅስቃሴያችን መሆን አለበት፡፡
- ሥራዎቻችን ወደኋላ እንዳይመለሱ ወጣቶች ተሰባስበው በሚገኙበት ቦታ ሁሉ መድረስ አለብን፡፡ ይህም በትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ በዩኒቨርስቲዎችና በመሳሰሉት ቢሆን ይመረጣል፡፡
- በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ሴቶች ቀን ሲሰሩ ውለው ማታ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱበት በርካታ ናቸው፡፡ ሥለዚህ በማታ ትምህርት በሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ላይ ተቀናጅተን መስራት ብንችል ውጤታማ እንሆናለን፡፡
- በወጣቶች መዝናኛ ማዕከል ላይ ወጣቶች ተዝናንተው በነፃነት የሚንቀሳቀሱበትን፣ ስለችግሮቻቸው የሚወያዩበትን ሁኔታ መፍጠር አለብን፡፡
- ሥራችንን ለመስራት የሚያመችን በተደራጁ ግዙፍ ማህበራት በኩል ብንገባ ነው፡፡ ዓላማችንን ከነሱ ጋር ካስተሳሰርን የተሻለ ሥራ መሥራት እንችላለን፡፡ ሥለዚህ ውስብስ በሆነው ቻናል ላይ መግባት ይጠበቃል፡፡ ኃላፊዎች ሥራችንን ስናቅድ በየትኛው መንገድ ውስጥ ብንገባ የተባለውን አካል መድረስ ይቻላል ብለን ማሰብ ይገባናል፡፡

- ሁሉም ሴክተሮች ከስትራቴጅያቸው አንፃር በመቀናጀት በጋራ አቅደው ቢሰሩ የተሻለ ሥራ መስራት ይቻላል፡፡
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስም የሚመጣውን ገንዘብ ለሌላ ዓላማ ማዋል አስቸጋሪ ስለሆነ በዚህ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ በኮንፈረንስ ሥም እየባከነ ያለውን ገንዘብ ልንገታ ይገባል፡፡
- ወደ 2.5 ሚሊዮን የሚሆኑ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶች ወደየአካባቢያችሁ መጥተዋል፡፡ ሥለዚህ እንድታግዟቸው እያሳሰብኩ እነዚህ ወጣቶች በቀጣይ ወደ ገቢ ማስገኛ ኘሮግራም የሚሰማሩ ይሆናል በማለት ሃሣባቸውን አጠቃለዋል፡፡

## <u>የመዝጊያ ንግግር በአቶ ያየህ አዲስ</u>

- በዚህ ሲምፖዝየም ላይ ውድ ጊዜያችሁን በመሰዋት የተሣተፋችሁ አካላትን እንዲሁም ለኘሮግራሙ እውን መሆን ከጐናችን ሁናችሁ ያበረታታችሁን አጋር አካላትን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ወደፊት ውጤት ለማምጣት የተቀናጀ ሥራ እንደምንሰራ እየተመኘሁ በክልሉ መንግስት ሥም መልዕክቴን ላስተላልፍ እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም ለዚህ ኘሮግራም እገዛ ላደረጉ ድርጅቶች የሽልማት ኘሮግራም ተካሂዶ ስብሰባው ከቀኑ በ6፡30 ላይ ተጠናቋል፡፡